- አሁን ከዮናስ የሚበልጠው ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡ እያስተማራቸው ነው።

- ከዮናስ የሚበልጠው ማን ነበር?
- አዳኙ አምላክ፣ ኢየሱስ።

- ኢየሱስ ከዮናስ የሚበልጠው እንዴት ነው?

- ዮናስ ሰው ብቻ ነበር ኢየሱስ ግን ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነበር።

- ኢየሱስ አዳኝ አምላክ ዮናስ ግን ሰው ብቻ ቢሆኑም፣ አይሁዶች በኢየሱስ ማመን አልፈለጉም።

- የኢየሱስ ትምህርት ከዮናስ ቢበልጥም፣ አይሁዶች ማመን አልፈለጉም።

- ኢየሱስ ዮናስ ሊያደርግ የማይችለውን ብዙ ተአምራዊ ምልክቶች ቢያደርግም፣ አይሁዶች በኢየሱስ ማመን አልፈለጉም።

- ኢየሱስ «አይሁዶች ከነነዌ ሰዎች የበለጠ ክፉዎች ናቸው» ያለው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም የነነዌ ሰዎች የዮናስን ትምህርት ሰምተው ንስሐ ገብተው፥ አይሁዶች ግን የአዳኙን አምላክ የኢየሱስን ትምህርት ሰምተው ንስሐ ስላልገቡ ነው።

- ኢየሱስ አይሁዶች ንስሐ እንዲገቡ ቢያስተምርም፥ ብዙ ተአምራዊ ምልክቶችንም ቢያደርግም፣ ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን አላመኑም።



## ትምህርት 53

1. ሽባው ሰው ራሱን መፈወስ ችሎአል?

ሀ- አልቻለም።

2. የሽባው ሰው ወዳጆች እርሱን ሊፈውሱት ችለዋል?

ሀ- አልቻሉም።

3. ሽባውን ሰው ማዳን የቻለ ሐኪም ነበር?

ሀ- አልነበረም።

4. ሰዎቹ ሽባውን ሰው ያመጡት ወደ ማን ነበር?

ሀ- ወደ ኢየሱስ።

5. ሽባውን ሰው ማዳን የቻለው ማን ብቻ ነበር?

ሀ- ኢየሱስ።

6. ኃጢአትን ይቅር ማለት የሚችል ሰው አለ?

ሀ- የለም።

7. ካህን ኃጢአትን ይቅር ማለት ይችላል?

ሀ- አይችልም።

8. ኢየሱስ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ማለት የሚችለው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

9. ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን ሊኖረው የቻለው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

10. የሌዊ ሁለተኛ ስሙ ማን ነበር?

ሀ- ማቴዎስ።

11. ኢየሱስ በጠራው ጊዜ የማቴዎስ ሥራ ምን ነበር?

ሀ- ማቴዎስ ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር።

ለ- ማቴዎስ ከራሱ ሕዝብ፣ ከአይሁዶች ቀረጥ እየሰበሰበ ለሮማውያን ይሰጥ ነበር።

12. ኢየሱስ ለፈሪሳውያን "ሕመምተኞች እንጂ ጤናማዎች ሐኪም አያስፈልጋቸውም" አላቸው። ኢየሱስ ምን ማለቱ ነበር?

ሀ- ኢየሱስ "ሕመምተኛ መሆናቸውን ያላወቁትን ሰዎች ላድን አልመጣሁም" ማለቱ ነበር።

13. ኢየሱስ የመጣው ማንን ሊያድን ነው?

ሀ- ኢየሱስ የመጣው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራታቸውንና እግዚአብሔር ብቻ ሊያድናቸው እንደሚችል ያመኑትን ሰዎች ሊያድን ነው።

- አንድ ቀን ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ኢየሱስ ተአምራዊ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት።

ማቴዎስ 12፡38

38- ከዚያም አንዳንድ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንና ፈሪሳውያን፣ «መምህር ሆይ፤ ከአንተ ታምራዊ ምልክት ማየት እንፈልጋለን» አሉት።



41- ኢየሱስ እንዲህ አለ «የነነዌ ሰዎች በፍርድ ዕለት ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ እነርሱ በዮናስ ስብከት ንስሓ ገብተዋልና። እነሆ፣ ከዮናስ የሚበልጥ እዚህ አለ።»

- ዮናስ ክፉ ወደሆኑት የነነዌ ሰዎች ሄዶ ንስሐ ካልገቡ እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው ተናገረ።

- የነነዌ ሰዎች ምን አደረጉ?

- በዮናስ አማካይነት የተነገራቸውን የእግዚአብሔር ቃል ሰምተው ንስሐ ገቡ።

- የነነዌ ሰዎች እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የሰጣቸውን የተስፋ ቃሎች ያውቁ ነበር?

- አያውቁም።

- የነነዌ ሰዎች እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ሕግጋት ያውቁ ነበር?

- አያውቁም።

- የነነዌ ሰዎች እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያደረጋቸውን ተአምራዊ ምልክቶች ያውቁ ነበር?

- አያውቁም።

- የነነዌ ሰዎች ከእነዚህ አንዱን እንኳን ባያውቁም ዮናስ ባስተማራቸው ጊዜ ንስሐ ገቡ።

- ኢየሱስ ለሰዎች «እሰጣቸዋለሁ» ያለው አንድ ብቸኛ ምልክት ምን ነበር?

- የዮናስ ምልክት።

- የዮናስ ምልክት ምን ነበር?

ማቴዎስ 12፥40

40- ኢየሱስ እንዲህ አለ «ዮናስ በዓሣ ዐንባሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ቆየ፣ እንዲሁ የሰው ልጅ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በምድር ሆድ ውስጥ ይቈያል።»

- የዮናስ ምልክት ምን ነበር?

- ዮናስ በትልቅ ዓሣ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ቆየ ሁሉ፣ ኢየሱስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በምድር ሆድ ውስጥ ይቆያል።

- ልክ እግዚአብሔር ዮናስን ከትልቅ ዓሣ ሆድ ውስጥ ከሦስት ቀንና ከሦስት ሌሊት በኋላ እንዳወጣው እንዲሁ፣ ኢየሱስንም ከምድር ሆድ ውስጥ ከሦስት ቀንና ከሦስት ሌሊት በኋላ ያወጣዋል።

- የዮናስ ምልክት ኢየሱስ አዳኙ እግዚአብሔር መሆኑን እንደሚያሳይ ኢየሱስ ለፈሪሳውያንና ለሕግ መምህራን ተናገረ።

- ኢየሱስ ለፈሪሳውያንና ለሕግ መምህራን ሌላ ምን አላቸው?

ማቴዎስ 12፥41



- ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን፥ የእግዚአብሔርን ቃል ከማመን ይልቅ ምን ለማየት ፈለጉ?

- ተአምራዊ ምልክት ማየት ፈለጉ።

- ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ተአምራዊ ምልክት ለማየት የፈለጉት ለምን ነበር?

- ኢየሱስ አጋንንትን ማውጣቱን አይተውና ሰምተው ነበር?
- አዎን።

- አይተዋል ሰምተዋል።

- ኢየሱስ ለምጻም መፈወሱን አይተውና ሰምተው ነበር?
- አዎን።

- አይተዋል ሰምተዋል።

- ኢየሱስ ሽባውን ሰው መፈውሱን አይተው ነበር?
- አዎን።

- አይተዋል ሰምተዋል።

- ኢየሱስ ወደ እርሱ የመጡትን ሕመምተኞች ሁሉ መፈወሱን አይተውና ሰምተው ነበር?

- አዎን።

- አይተዋል ሰምተዋል።

- ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ተጨማሪ ተአምራዊ ምልክቶችን ለማየት የፈለጉት ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ኢየሱስ አዳኙ አምላክ መሆኑን ስላላመኑ ነበር።

- በኢየሱስ ከማመን ይልቅ ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ተአምራዊ ምልክቶችን ብቻ ለማየት ፈለጉ።

- በእግዚአብሔር ቃል ከማመን ይልቅ ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ተአምራዊ ምልክቶችን ብቻ ለማየት ፈለጉ።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ብዙ ተአምራዊ ምልክቶችን ቢያሳያቸውም፣ በእግዚአብሔር አለማመናቸውን ታስታውሳላችሁ?

- እግዚአብሔር አሥር መቅሰፍቶችን በፈርዖንና በግብፃውያን ላይ ቢያወርድባቸውም፣ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር አላመኑም።

- እግዚአብሔር ፈርዖንንና ሠራዊቱን በቀይ ባሕር ውስጥ ቢያሰጥማቸውም እስራኤላውያን በእግዚአብሔር አላመኑም።

- እግዚአብሔር በምድረ በዳ ድርጭትና መና ቢልክላቸውም እስራኤላውያን በእግዚአብሔር አላመኑም።

- ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ከማመን ይልቅ ተአምራዊ ምልክቶችን ብቻ ለማየት ይፈልጋሉ።



- ተአምራዊ ምልክቶችን ማየት ያድነናል?

- አያድነንም።

- የሚያድነን በአዳኙ ኢየሱስ ማመን ብቻ ነው።

- «በኢየሱስ የምናምነው ተአምራዊ ምልክት ካየን ብቻ ነው» ካልን ምን ማለታችን ነው?

- «ኢየሱስ ውሸታም ነው» ማለታችን ነው።

- «የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን የምናምነው ተአምራዊ ምልክት ካየን ብቻ ነው» ካልን፣ ምን ማለታችን ነው?

- «የእግዚአብሔር ቃል ውሸት ነው» ማለታችን ነው።

- ኢየሱስ ለፈሪሳውያንና ለሕግ መምህራን ምን መለሰላቸው?

ማቴዎስ 12፡39

39- ኢየሱስ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይጠይቃል፤ ነገር ግን ከነቢዩ ዮናስ ምልክት በስተቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም።»

- ኢየሱስ ምን አለ?

- ኢየሱስ «ክፉና አመንዝራ ትውልድ ብቻ ምልክት ይጠይቃል» አለ።